የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች

## ዝርዝር መመሪያ

□□□ 181/2013

# ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች
# ለመወሰን የወጣ ዝርዝር መመሪያ

ወጣቱ ትውልድ የነገው አገር ተረካቢ ዜጋ ከመሆኑም ባሻገር ለሀገሪቱ ፈጣን ልማትና እድገት የላቀ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ወሳኝ የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ወጣቱ የነገውን ሀገራዊ ሀላፊነትና አደራ በሚገባ ለመወጣት እንዲችል በመልካም አስተዳደግ ፣ በስነምግባር፤በትምህርትና ስልጠና ተቀርጾ እውቀትና ክህሎት ያለው፤ ጤንነቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ስብዕናው የተሟላ ፣ ለሀገርና ለህዝብ ሁለንተናዊ እድገትና ልማት የሚጠቅም ብቁ ዜጋ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለሆነም በኢትዮጵያ የተፋጠነ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ወጣቶች ያላቸውን የተጠናከረ ተሳትፎና ወደፊትም የሚኖራቸውን የጎላ ድርሻ ከግንዛቤ በማስገባት፣

- በስራ ላይ ሲሰማሩ ከተለያዩ የስራ ላይ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች እንዲጠበቁ ማድረግና እና
- ከባድና አካላዊ ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ አደገኛ ስራዎችና የስራ ሁኔታዎች መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

የኢፌዲሪን ህገመንግስት መሠረት ማድረግ ፣ ሀገሪቱ ከምትመራበት የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲ ጋር በማጣጣምና ከአለም አቀፍ ስምምነቶችጋር በማገናዘብ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አፈፃፀምን ለማጐልበት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክር በማድረግ ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 89(4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር ለመወሰን የወጣ መመሪያ 181/2013; □□□ □□□□ □□□□□□□

## 3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. **"አሠሪ"** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2(1) የተሰጠ ትርጉም ነው፡፡
2. **"ወጣት ሠራተኛ"** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 89(1) የተሰጠ ትርጉም ነው፡፡
3. **"ሚኒስቴር"** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/1996 አንቀጽ 2/4 የተሰጠ ትርጉም ነው፡፡
4. **"ተከታታይነት ያለው ሥራ"** ማለት የሥራው እንቅስቃሴ የመቋረጥ ባሕሪይ የሌለበት እና የድግግሞሽ ሂደት የሚታይበት ሆኖ አካላዊ ጫና የሚያስከትል ወጥነት ያለው የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡
5. **"አደገኛ ሥራዎች"** ማለት በባሕሪያቸው ለሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት አስጊ የሆኑ በጥሬ ዕቃነት፣ በተጨማሪ ግብአትነት፤ በምርትነትና በተረፈ ምርትነት የሚያገለግሉ ወይም በአሠራሩና በሥራው ሁኔታ የተነሳ የሚከሰቱ የአደጋና የጤና ጉዳት ስጋቶች ያሉባቸው ሥራዎችና የሥራ ዘርፎች ናቸው፡፡
6. **"አደገኛ ኬሚካሎችና ንጥረ ነገሮች"** ማለት ባላቸው ፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ንጥረነገር ይዘት በሰውና በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ቁሶች ናቸው፡፡
7. **"ኃላፊነት የተሰጠው ባለሥልጣን"** ማለት የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ.691/2001 መሠረት ነው፡፡
8. **"ከባድ ሥራ"** ማለት በደቂቃ ከ7.0 ኪሎ ካሎሪ በላይ የሆነ ሜታቦሊክ ኢነርጂ ወይም ጉልበት የሚጠይቅ የሥራ እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

9. **"ከመሬት በታች የሚካሄድ የቁፋሮ ሥራ"** ማለት ከመሬት በታች በመሳሪያና በእጅ ከሚደረግ የማዕድን ቁፋሮ እና ፍለጋ ጋር የተያያዙ ሥራዎች ማለት ነው፡፡
10. **"ጨረራ"** ማለት ማንኛውም የውስጥ አካልና ህዋስን ሰንጥቆ የማለፍ ሃይል ያለው የኤሌክትሮ ማግኔትክ ሞገድ ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/96 በሚሸፍናቸው አሠሪዎችና ወጣት ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5. ወጣት ሠራተኞች እንዳይሰማሩባቸው የተከለከሉ ሥራዎች

1. የወጣት ሠራተኞችን ሕይወት፣ ደህንነትና ጤንነት ለአደጋ የሚያጋልጡ ሥራዎች እና የሥራ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው፡፡
   - ሀ መንገደኞችንና ዕቃዎችን በመንገድ ፣በባቡር፣ በአየርና በአገር ውስጥ ውሃዎች የማጓጓዝ ሥራ፣
   - ለ በወደቦችና በመጋዘኖች የሚሰራ ከባድ ዕቃ ማንሣት መጎተት ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ የጉልበት ሥራ፤
   - ሐ በባህርና በውሃ ላይ የጉዞና የዓሳ ማስገር እንዲሁም ጭነትን የማጓጓዝ ሥራዎች፣
   - መ ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች፣ ከኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና ከማከፋፈያ ጣቢያዎች ጋር ግንኙነት ያለው ሥራ፣
   - ሠ ከመሬት በታች በሚካሄዱ የማዕድን ቁፋሮ ፣ የድንጋይ ካቦዎችና የመሳሰሉት ሥራዎች ፣
   - ረ ከከፍታ ቦታ ላይ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራ በርብራብ/ስካፎልዲንግ/ መሥራት ፣ ዕቃን ከታች ወደ ላይ በመሣሪያ ተጠቅሞ ማንቀሳቀስ ፣ እንዲሁም በኤሌክትሪክ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

ክሬኖችና ሊፍቶች በመጠቀም ዕቃን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የማንቀሳቀስ ሥራዎች፣

ሰ የዋሻ ቁፋሮ ሥራዎች፣

ሸ የአልኮል መጠጥ፣ ሲጋራና ሌሎች ሱስ የሚያሲዙ ንጥረ ነገሮችን የማምረትና የመሳሰሉ ሥራዎች፣

ቀ እጅግ በጣም ቀዝቃዛ የሆኑ ማከማቻ መጋዘኖችና የሥራ ክፍሎች ውስጥ መስራት፣

በ ከፍተኛ የሙቀት ጫና ያለባቸው የስኳር ፋብሪካዎች፣ የብረታ ብረት ማቅለጫዎች ውስጥ መስራት፣

ተ ጎጂ ለሆኑ የአዮናይዚንግና አዮናይዚንግ ያልሆኑ (የኤክስሬይ ፣ አልትራቫዮሌት ፣ ጋማሬ ፣ ቪዚብል ወዘተ) ጨረሮች የሚያጋልጡ ሥራዎች

ቸ አደገኛና መርዘኛ የሆኑ ኬሚካሎችን ማለትም አርሴኒክ፣ ሊድ፣ ሜሪኩሪ፣ ካድሚየም፣ ማንጋኒዝ፣ሳያናይድና የመሳሰሉ ብረታማ ንጥረ ነገሮችና አሟሚዎች ሥራ ላይ በሚውሉበት የሥራ ዘርፍ፣

ኀ የተቀጣጣይነትና የፈንጂነት ባህሪ ያላቸው ንጥረ ነገሮች በሚመረቱባቸውና አገልግሎት ላይ በሚውሉባቸው ሥራዎች፣

ነ የተለያዩ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የማዘጋጀት፣የመበጥበጥና የመርጨት፣ ሥራዎች፣

ኘ ተላላፊ በሽታዎችን የሚያስከትሉ ስነ ህይወታዊ ጠንቆች ማለትም ከፈንገስ፣ ከባክቴሪያና ቫይረስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች መሥራት፣

አ ለወጣት ሠራተኞች አካላዊና አእምሮአዊ ዕድገት እንዲሁም ሞራል ላይ ጉዳት የሚያስከተሉ ሌሎች ሥራዎች፣

## 6. መመሪያው ተፈፃሚ የማይሆንባቸው የሥራ ዘርፎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩ ሥራዎች ኃላፊነት የተሠጠው ባለሥልጣን ባፀደቀውና በሚቆጣጠረው የትምህርትና የሙያ ማሠልጠኛ ተቋሚት በሚሰለጥኑና ልምምድ በሚያደርጉ ወጣቶች ላይ መመሪያው ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## 7. ለወጣት ሠራተኞች የተወሰነ የክብደት  መጠን

1. የወጣት ሠራተኞችን ጉልበት በመጠቀም የሚካሄድ ማናቸውም ክብደትን ከቦታ ቦታ የማንቀሳቀስ፣ የመሸከም፣ የሚጓጓዝ፣ የማንሳት፣ የማዉረድ፣ የማውጣት፣ የመጎተት፣ የመሳብና የመሳሰሉት ሥራዎች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን የክብደት መጠን ጣሪያ ሳያልፉ ይከናወናሉ፡፡

   ሀ. እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ በእጅ ሆኖ፣

   1. ተከታታይነት ላለው ሥራ የዕቃው ክብደት እስከ 7 ኪሎ ግራም
   2. ተከታታይነት ለሌለው ሥራ የዕቃው ክብደት እስከ 11 ኪሎ ግራም

   ለ. እንቅስቃሴ ሙሉ  በሙሉ በእጅ ሆኖ ዳገት የመውጣትና የመወረድ ሁኔታ ከታከለበት፣

   1. ተከታታይነት ላለው ሥራ የዕቃው ክብደት እስከ 5 ኪሎ ግራም
   2. ተከታታይነት ለሌለው ሥራ የዕቃው ክብደት እስከ 9 ኪሎ ግራም

   ሐ. እንቅስቃሴው ባለ አንድ እግር ጋሪ ሆኖ

   1. ወለሉ ባልተስተካከለ ንጣፍ የዕቃው ክብደት እስከ 16 ኪሎ ግራም
   2. ወለሉ በተስተካከለ ንጣፍ የዕቃው ክብደት እስከ 20 ኪሎ ግራም

## 8. ስለ ኃላፊነት

ማንኛውም አሠሪ፣

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ክልከላ በተደረገባቸው ሥራዎችና የሥራ ዘርፎች ውስጥ የተሰማሩ ወጣት ሠራተኞች ካሉ ደመወዛቸው ሳይቀነስ ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ የማሰራትና የጤና ጉዳት ያለመከሰቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. ወጣት ሠራተኛን ከመቅጠሩ በፊት በራሱ ወጪ ከኤች. አይ. ቪ ምርመራ በስተቀር የጤና ምርመራ ማድረግና መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡
3. በዚህ መመሪያ ከተከለከሉ ሥራዎችና የስራ ዘርፎች ውጭ ባሉ የሥራ መደቦች ላይ ለተቀጠሩ ወጣት ሠራተኞች ተገቢውን የነፍስ ወከፍ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች በነፃ የማቅረብ፣ አጠቃቀሙን የማሰልጠን፣ የመቆጣጠርና የሥራ ላይ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል የጥንቃቄ መረጃና ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

4. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚሰጡ ትዕዛዞችን ተፈጻሚ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፡፡
5. አሠሪው የዚህን መመሪያ አፈፃፀም አስመልክቶ ለሚኒስቴሩ በየሩብ ዓመት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 9. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የሚመለከተው አካል ወይም ግለሰብ ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 10. ቅጣት

ይህ መመሪያ የሚመለከተው ማንኛውም አሠሪ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ድንጋጌዎችን ቢጥስ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ስለቅጣት የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡

## 11. መመሪያውን ስለ ማሻሻል

ሚኒስትሩ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በየወቅቱ እየገመገመ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 12. የተሻረ መመሪያ

ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ሥራዎች ዝርዝር መመሪያ ለመወሰን ነሐሴ 11 ቀን 1989 ዓ.ም. የወጣው መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 13. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ 25 ሚያዝያ 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር